የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ

DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA

OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| ፪ኛ ዓመት ቁጥር ፲፪<br>አርባምንጭ ታህሳስ ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ዓ.ም | በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 2nd year No 12<br>Arba Minch December 15th 2023 |


| መውጫ | Content |
|---|---|
| አዋጅ ቁጥር ፲፭/፪ሺ፲፮<br>የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት በየደረጃው የሚገኙ የምክር ቤት ተወካዮች ብዛት ለመወሰን የወጣ አዋጅ --ገፅ | Proclamation No. 15/2023<br>The South Ethiopia Regional State to Determine the Number of Representatives in the Councils at All Level Proclamation----Page |

| | |
|---|---|
| **አዋጅ ቁጥር ፲፭/፪ሺ፲፮**<br>**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት በየደረጃው የሚገኙ የምክር ቤት ተወካዮች ብዛት ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፭/፪ሺ፲፮** | **Proclamation No. 15/2023**<br>**The South Ethiopia Regional State to Determine the Number of Representatives in the Councils at All Level Proclamation 15/2023** |
| **መግቢያ** | **Preamble** |
| በክልሉ በየደረጃው የሚገኙ የምክር ቤት አባላት ምርጫ በአግባቡ እንዲካሄድ የቅድመ ዝግጅት ስራ በጥራት ማከናውን አስፈላጊ በመሆኑ፣ | Whereas it is found necessary to carry out preparatory work in a quality manner so that the election of council members at all level of the region to be conducted properly, |
| የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነምግባር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፪/፪ሺ፲፩ መሰረት ክልሎች በየደረጃው የሚገኙ የምክር ቤት አባላት ብዛትን እና በአንድ ምርጫ ክልል ወይም አካባቢ ምን ያህል ተወካዮች እንደሚመረጡ በህግ የመወሰን ስልጣን የተሰጣቸው በመሆኑ፤ | Whereas, pursuant to the Ethiopian Elections, Political Parties Registration and Electoral Ethics Proclamation No. 1162/2019, regional states are legally empowered to determine the number of council members at each level and how many representatives will be elected in a constituency or area; |
| የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ም/ቤት በክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ አንቀጽ ፶፬ ንዑስ አንቀጽ ፫ (ሀ) ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል። | Now, therefore, the South Ethiopia Regional State Council has enacted this proclamation in accordance with its powers enshrined under article 54 Sub-Article 3(a) of the State Constitution. |

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት በየደረጃው የሚገኙ የምክር ቤት ተወካዮች ብዛት ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፭/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ

፩."የምርጫ ክልል" ማለት በምርጫ አዋጁ በአንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ ፲፭ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

፪."በየደረጃው የሚገኝ ም/ቤት" ማለት የክልል የዞን፡ የወረዳ፤ የከተማ እና የቀበሌ ም/ቤት ነው፡፡

፫."የምርጫ አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፪/፪ሺ፲፩ ነው፡፡

፬."ተወካይ" ማለት በየአካባቢው የምርጫ ክልል ተመርጦ በየደረጃው ባለ ምክር ቤት የሚገኝ ተወካይ አባል ነው፡፡

፭."ልዩ ተወካይ" ማለት በክልሉ የሚገኙ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች የተለየ ውክልና የሚያስፈልጋቸው ብሄሮች፤ ብሄረሰቦች በአንድ የምርጫ ክልል ወይም አካባቢ ለመወከል የሚመረጥ የክልል ም/ቤት፤ የዞን ም/ቤት ተመራጭ ወይም ተወካይ አባል ነው፡፡

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

'' This proclamation may be cited as " The South Ethiopia Regional State Council Number of Representatives at Each Level Determination Proclamation No. 15/2023 "

### 2. Definitions

In this Proclamation

1. "Electoral Area" has the meaning given in Article 2, Sub-Article 15 of the Electoral Proclamation.
2. "State Council at each level" means a regional, zonal, woreda, city and kebele Council.
3. "Electoral Proclamation" means the Ethiopian Election, Political Parties Registration and Election Ethics Proclamation No. 1162/2019.
4. "Representative" means a representative member of a council at each level elected from a regional constituency.
5. "Special Representative" means a member of a State Council or Zonal Council elected to represent nations, nationalities and peoples in a region who require special representation; nations and nationalities in a region who are elected to represent a single constituency or area.

**፫. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ በክልሉ በየደረጃው በሚገኙ የምርጫ ክልልና አካባቢዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## በየደረጃው ምክር ቤት ተወካዮች ብዛት

**፬. ስለተወካዮች ብዛት**

፩.የክልል ም/ቤት አባላት ምርጫ በአንድ መደበኛ የምርጫ ክልል ፭ ተወካዮች እንዲሁም በልዩ ምርጫ ክልል ፪ ተወካዮች ይመረጣሉ፡፡

፪.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በምርጫ ሕጉ መሠረት የተለየ ውክልና የሚያስፈልጋቸው ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ለክልል ም/ቤት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተጨማሪ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፫.የዞን ም/ቤት ለክልል ም/ቤት የሚመረጡትን አባላት ሳይጨምር በአስተዳደሩ ከታቀፉት ወረዳዎች ውስጥ እስከ ፬ መዋቅር (ወረዳ/ከተማ) ባላቸው ዞኖች ከእያንዳንዱ ወረዳ/ከተማ በነፍስ ወከፍ ፲፭ ተወካዮች፣ ከ፭ — ፲ መዋቅር (ወረዳ/ከተማ) ባላቸው ዞኖች ከእያንዳንዱ ወረዳ/ከተማ በነፍስ ወከፍ ፲፪ ተወካዮች፣ እንድሁም ፲፩ እና በላይ መዋቅር (ወረዳ/ከተማ) ባላቸው ዞኖች ከእያንዳንዱ ወረዳ/ከተማ በነፍስ ወከፍ ፲ ወክሎች የሚወከሉበት ይሆናል፡፡

**3. Scope of Application**

This Proclamation shall apply to the constituencies and areas at all levels of the Region.

## Part Two
## Number of Representatives in the Council at Each Level

**4. Number of Representatives**

1. In the election of members of the Regional Council, 5 representatives are elected from a regular constituency and
2. Without prejudice to the provisions of Sub-Article 1 of this Article, additional representation may be granted to the Regional Council if deemed necessary, for nations, nationalities and peoples that require special representation in accordance with the Electoral Law.
3. In the zones comprising the administrative districts with up to 4 structures (Woreda/Ketema), excluding the members elected to the Regional Council, 15 representatives per capita from each Woreda/Ketema; in the zones with 5-10 structures (Woreda/Ketema), 12 representatives per capita from each Woreda/Ketema; Also, in zones with 11 or more structures (Woreda/City), 10 representatives will be represented from each Woreda/City.

፩.በዞን ምክር ቤት ያልተወከሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች የሚኖሩ ከሆነ ፪ ተወካዮች በልዩ ውክልና እንድሳተፉ ይደረጋል፡፡

፭.ለወረዳ ም/ቤት ወረዳው ከተደራጀበት አካባቢ የሚወከሉ ሆነው ፲ እና ከ፲ በታች ቀበሌዎች ከያዘ ከእያንዳንዱ ቀበሌ ፲ አባል የሚወከል ሲሆን ከ፲፩ — ፳፬ ቀበሌዎች የያዜ ወረዳ ደግሞ ፱ አባል የሚወከል እንድሁም ከ፳፭ በላይ ቀበሌዎች ከያዜ ወረዳ ከእያንዳንዱ ቀበሌ ፭ አባል የሚወከል ይሆናል፡፡

፮.ለከተማ አስተዳደር ም/ቤት በየደረጃ ያሉ የከተማ አስተዳደሩ ም/ቤት ተወካይ አባላት እንደሚከተለው ይሆናል፤

ሀ)ለሬጅዮፖሊስ ከተማ አስተዳደር ም/ቤት አስተዳደሩ ከተደራጀበት ከእያንዳንዱ ቀበሌ ፲ ተወካዮች የሚወከሉ፤ እና ከተማው ከሚገኝበት ዞን በልዩ ውሳኔ የሚወከል ፲ አባላት እንዲሁም በዚሁ ምርጫ ክልል የምክር ቤት ፭ አባላት በቀጥታ የሚሳተፉ ይሆናል፡፡

ለ)ለፈርጅ አንድ ከተማ አስተዳደር ም/ቤት አስተዳደሩ ከተደራጀበት ከእያንዳንዱ ቀበሌ ፲፭ ተወካዮች እና ከአጎራባች ፲፭ አባላት የሚወከሉ ይሆናል፡፡

4. If there are nations and nationalities that are not represented in the Zonal Council, 2 representatives will be allowed to participate through special representation.

5. For the Woreda Council, if the Woreda has 10 or less kebeles, 10 members will be represented from each kebele, and for the Yaze Woreda with 11-24 kebeles, 9 members will be represented, and for the Yaze Woreda with more than 25 kebeles, 5 members will be represented from each kebele.

6. For the City Administration Council, the representatives of the City Administration Council at each level will be as follows;

a) For the Regiopolis City Council, 10 representatives will be represented from each kebele where the administration is organized; and 10 members who shall be represented by special resolution from the zone where the city is located, as well as 5 members of the council in the same constituency who shall participate directly.

b) For the Category One City Council, 15 representatives will be represented from each kebele where the administration is organized and 20 members from neighboring kebeles.

ሐ) ለፌርጅ ሁለት ከተማ አስተዳደር ም/ቤት የከተማ አስተዳደሩ ከተደራጀበት ከእያንዳንዱ ቀበሌ ፳ ተወካዮች እና ከአጎራባች ፳ አባላት ይወከላሉ፡፡

መ)ለፌርጅ ፫ ከተማ አስተዳደር ም/ቤት ከተማ አስተዳደሩ ከተደራጀበት ከእያንዳንዱ ቀበሌ ፳፭ እና ከአጎራባች ፳ አባላት የሚወከል ይሆናል፡፡

፯.በየደረጃው ለሚገኘው የገጠር እና የከተማ ቀበሌዎች በቀጥታ ፻፳ ተወካዮች እንድወከሉ ይደረጋል፡፡

## ፭. ስለተወካዮች ብዛት ለውጥ

፩.በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ስር የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ ምክር ቤት በክልሉ በየትኛውም ደረጃ በሚገኙ ተወካዮች ብዛት ላይ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የእጩዎች ምዝገባ ከመካሄዱ በፊት ለምርጫ ቦርድ በማሳወቅና ስፈቀድ በማናቸውም ጊዜ ሊለውጠው ይችላል፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ስር የተደነገገው መሰረት የተደረገውን የተወካዮች ብዛት ለውጥ ለብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

c) For the Category two City Council, 20 representatives will be represented from each kebele where the city administration is organized and 20 members from neighboring kebeles.

d) For the Category 3 City Council, 25 representatives will be represented from each kebele where the city administration is organized. and 20 members from neighboring kebeles.

7. 120 representatives will be directly represented for the rural and urban kebeles at each level.

**5. Changes in the Number of Representatives**

1. Notwithstanding the provisions of Article 4 of this Proclamation, the Regional Council may, if it deems it necessary to make adjustments to the number of representatives at any level in the Region, change it at any time by notifying the Election Board before the commencement of candidate’s registration.

2. The change in the number of representatives made in accordance with the provisions of Sub-Article 1 of this Article shall be notified to the Office of the National Election Board.

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፮. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ አፈፃፀም እና ትግበራ መተባበር አለበት፡፡

### ፯. ደንብና መመሪ ያ የማውጣት ስልጣን

የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚረዳ ደንብ እና መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### ፰.ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

በዚህ አዋጅ ከተመለከቱ ጉዳዮች ጋር የሚቃረን ማንኛዉም ሕግ እና አሰራር ተፈፃሚነት የለውም፡፡

### ፱. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከጸደቀበት ታህሳስ ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አርባ ምንጭ ታህሳስ ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ጥላሁን ከበደ**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ርዕሰ መስተዳድር**

## Part Three

## Miscellaneous Provisions

### 6. Obligation to Cooperate

Any person shall have a duty to cooperate in the implementation and enforcement of this Proclamation.

### 7. Power to Issue Regulations and Guidelines

The Regional Executive Council may issue regulations and directives in the implementation of this Proclamation.

### 8. Inapplicable Laws

Any law or procedure that is inconsistent with this Proclamation shall be inapplicable.

### 9. Effective Date

This proclamation shall come into force on December 15th, 2023, from the date of its approval by the Regional Council.

**Done at Arbaminch, On this Day of 15th December , 2023**

**Tilahun Kebede**

**Chief Executive of The South Ethiopia Regional State**